Reçu CLT / CIH / ITH

Le 24 JUIL. 2014

N° ......0555......

0095300042

# የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ (ኢ.ባቅ) በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመመዝገብ የተዘጋጀ የኢንቬንተሪ ፎርማት

(Format for National Register of the Intangible Cultural Heritage of Ethiopia)

መለያ ቁጥር- 0002

Register No-0002

## 1. ዳራ (Background)

የሐረሪ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ከተዋቀሩት አስር ክልሎች አንዱ በሆነው የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት መቀመጫ በሆነችው እና በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት በተመዘገበችው ታሪካዊቷ የሐረር ጁጎል እና በዋናነት የሚኖር ሕዝብ ሲሆን በሐረር ከተማ፣ በድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በምስራቅ ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ስፍራዎችም ሰፍሮ ይገኛል፡፡

በዋናነት መኖሪያቸውን በከተሞች ያደረጉት የሐረሪ ብሔረሰብ ዓባላት በንግድ፣ በመንግሥት ስራ እና በግብርና ህይወታቸውን የሚመሩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የብሔረሰቡ ሴቶች በተለይም እናቶች ልዩ ልዩ የእደጥበብ ምርቶችን በመስራትና ለገበያ በማቅረብ ሕይወታቸውን የሚመሩ ሲሆን በተለይም ከስንደዶ የሚሰፉዋቸው እንደ ሐማት ሞትና የመሳሰሉ የስፌድ እቃዎች የብሔረሰቡ መለያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

የሐረሪ ብሔረሰብ በሰፈረበት መልክዓምድር ባሳለፋቸው የዘመናት መስተጋብሮች የፈጠራቸው በርካታ ግዙፍነት ያላቸው (የሚዳሰሱ) እና ግዙፍነት የሌላቸው(የማይዳሰሱ) /tangible and intangible/ ባህላዊ ቅርሶችን ያፈራ ሲሆን በተለይም በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን እንደተገነባ በታሪክ የተረጋገጠውን የሐረር ጁጎል ግንብ ለዓለም በቅርስነት ያበረከተ ሕዝብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ብሔረሰቡ ከሚዳሰሱ ቅርሱ ባልተናነሰ በርካታ የማይዳሰሱ /intangible/ ቅርሶች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶቹ መካከልም ዓመታዊ ክብረ በዓላት ለምሳሌ ያህል እንደ ሸዋል ኢድ፣ ጁማቱል በርኸድሌ፣ ዊርሻቶ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደ አፎቻ ያሉእርስ በእርስ የሚረዳዳባቸው ማህበራዊ ተቋማት ያሉት ሲሆን ብሔረሰቡ ከዚህም ሌላ የራሱ የሆነ የጋብቻ ባህልና፣ የባህላዊ ቤት አሰራርና አደረጃጀት እራሳቸውን የቻሉ ድንቅ የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶቹ መገለጫዎች ናቸው፡፡ የዚህ የሀገር አቀፍ የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ ኢንቬንተሪ ርእስ የሆነው ዊርሻቶ /ባህላዊ ጭፈራ/ ከቅል ሰበራ ፣ የብሄረሰቡ አባላት በቤተሰብ ደረጃ እና ከጎረቤቶቻቸው ጋር በጋራ ገንፎ ከመብላት እንዲሁም ጅቦችን በተለያዩ አድባራት/አዋቾች/ ከማብላት ባሻገር በሐረር ከተማ የሚገኘው የሐረሪ ብሔረሰብ እና በከተማዋ ዙሪያዋ የሚገኙት የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች መገለጫ ጭምር ነው፡፡

ዊርሻቶ መልካም የሆኑ ስነምግባሮች የሚወደሱበት እና የቀደምት አባቶች አርአያነት የሚወሳበት እንዲሁም ለመልካም ስነምግባር ተጻራሪ የሆኑ ተግባራት የሚወገዙበትና የሚኮነኑበት ተምሳሌታዊ የብሔረሰቡ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ በመሆኑ በአግባቡ ቢጠበቅና ቢለማ ከብሔረሰቡ አልፎ ለሀገር እና ብሔረሰቡ አብሮ ለሚኖራቸው ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር የራሱን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል ባህላዊ እሴት ነው፡፡

ይህ በመለያ ቁጥር 0002 በብሔራዊ ኢንቬንተሪ የተካተተው ዊርሻቶ/ባህላዊ ቍፈራ/ እና ተያያዥ ሥነ-ሥርዓቶች ከሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ የአስቸኳይ ጊዜ ጥበቃ የሚፈልጉ ዝርዝር /For Inscription on the List of Intangible Cultural Heritage in Need of Urgent Safeguarding in 2014/ ውስጥ እ.ኤ.አ በ2014 ለማስመዝገብ ያቀረበችው ቀዳሚው ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ ነው፡፡

## 2. የኢንታንጀብል ቅርሱ መረጃ፣-

### 2.1 የቅርሱ ምድብ (Domain)

ማኅበራዊ ክንዋኔዎች፣ ሥነ-ሥርዓቶችና ፌስቲቫሎች (Social practices, rituals and festive events) ነው፡፡

### 2.2 የቅርሱ መጠሪያ በብሄረሰቡ/በቡድኑ ቋንቋ( **Name of the element, as used by community or group concerned)**

ዊርሻቶ- የሐረሪ ብሔረሰብ ባህላዊ ቍፈራ፣ የቅል ሰበራ እና ጅቦችን ገንፎ የማብላት ክብረ በዓል

### 2.3 Wirshato- Gourd Smashing, Porridge feeding to people and hyena porridge feeding celebration among the Harari in Ethiopia

### 2.4 የቅርሱ ባለቤት ብሔረሰብ፣ ቡድን ወይም ግለሰብ( **Community(ies),group(ies) or individuals concerned** )፡-

የሐረሪ ብሔረሰብ

Harari People

### 2.5 ስለ ቅርሱ ምንነት ማብራሪያ(Description of the element):-

በሐረሪ ብሔረሰብ በየዓመቱ ከሚከበሩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት መካከል "ዊርሻቶ" የሐረሪ "የቁራን ጌይ" ተማሪዎችና የሐረር ከተማ ወጣቶች ባህላዊ ቍፈራ እና የቅል ሰበራ ሥነ ሥርዓት አንዱ ነው፡፡ ክብረ በዓሉ በዋናነት በሶስት ዋና ዋና ሥነ-ሥርዓቶች የሚከበር ነው፡፡ ቀዳሚው ለብሔረሰቡ ኢንታንጀብል

ባህላዊ ቅርስ መጠሪያ የሆነው ዊርሻቶ/ባህላዊ ጭፈራ/ "የቁራን ጌይ" ተማሪዎችና እና የከተማዋ ወጣቶች የበዓሉን ስንኞች እያሰሙ የሚጨፍሩበት እና ቅል የመስበር ሥነ-ሥርዓት የሚያከናውኑበት፣ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት የብሔረሰቡ አባላት ለአስር ቀን ከጾሙ በኋላ ጾም በሚፈቱበት እለት ዘመድ አዝማድና ጎረቤት ተሰባስቦ ገንፎ/ሹ-ር/ ተገንፍቶ በጋራ የሚመገቡበት እና ክምስር፣ አተር፣ ሽምብራ፣ ስንዴ እና ሌሎችም እህሎች ተቀይጦ ከተዘጋጀ ዱቄት ጅቦችን በተለያዩ አድባራት ገንፎ የሚያበሉበት ሥነ-ሥርዓት የሚከናወንበት ደማቅ ክብረ በዓል ነው፡፡

ይህ ክብረ በዓል በብሔረሰቡ አባላት ለረጅም ዘመናት ሲከበር ቆይቷል፡፡ ክብረ በዓሉ ለመከበሩ መነሻ ከሆኑት ሀይማኖታዊ ምክንያቶች አንዱ ነብያት ከተለያዩ አደጋዎች የዳኑበትና የአላህ መልእክተኞች ልዩ ችሎታ ከፈጣሪ ያገኙበት ቀን በመሆኑ ይህንኑ ለመዘከር በሚል እንደሚያከብሩት ይነገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለክብረ በዓሉ መከበር እንደ መነሻ ከሚጠቀሱት ማህበራዊ ምክንያት ተጠቃሹ በቀደመው ዘመን በከተማዋ ከእስልምና ሀይማኖት እሴቶችና ትዕዛዛት ተጻራሪ የሆነው ጠጪነት መስፋፋቱን ተከትሎ የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች መከሰታቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህን ወቅት የከተማዋ አሚር በከተማዋ በሚዘዋወሩበት አንድ ኢጋማሚ አንዲት ሴት በጀርባዋ ህጻን አዝላ ይመለከቱና ባደረጉት ማጣራት ልጅቷ በመጠጥ ሀይል በስከረ የራሷ ልጅ ተደፍራ መውለዷን በመረዳታቸው መሰል ማህበራዊ ቀውሶች በከተማዋ እንዳይደገሙ በማሰብ በከተማዋ መጠጥ መጠጣትና መስከርን የሚከለክል አዋጅ ያስነግራሉ፡፡ አዋጁን ተከትሎም ቀደም ሲል ለመጠጥ ማዘጋጃነት ያገለግሉ የነበሩ እቃዎችን ህብረተሰቡ ከየቤቱ እያወጣ ይሰባብራል፡፡ ይህ የሰበራ ሥነ-ሥርዓት የተፈፀመበት እለት ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ነብያት ከተለያዩ አደጋዎች ከዳኑበትና የአላህ መልእክተኞች ልዩ ችሎታ ከፈጣሪ ያገኙበት ቀን ከሚዘከርበት እለት ጋር በመገጣጠሙ ከዛን ጊዜ ጀምሮ በያመቱ የመጠጥ ጋኖችን በመስበርና መጠጥና ስካር የሚያስከትሏቸውን ማህበራዊ ጠንቆች በዜማና ጭፈራ ማውገዝ እንደባህል መለመዱ ይነገራል፡፡ የኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች በየትውልዱ እየዳበሩ እና አዳዲስ ነገሮችን እያከሉ እንዲሁም ከተፈጥሮ ጋር በሚደረጉ መስተጋብሮች እራሳቸውን ማስተካከላቸው ተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው በመሆኑ ቀደም ሲል በእለቱ ጋኖችን በመሰባበር ይፈፀም የነበረው ሥርዓት ቅል (gourd) በመስበር መተካቱ እና ይኸው ሥነ-ሥርዓት ለረጅም ዘመናት ሲተገበር እንደነበረ እና አሁን አሁን በልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ለውጦች የተነሳ ቅሉን እንደልብ ማግኘት ሲቸግር ህጻናቱ የፕላስቲክ እቃዎችን በመምታት ሥነ-ሥርዓቱ እየተተገበረ እንደሚገኝ መረዳት ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል በነበረው የክብረ በዓሉ አተገባበር "የቁራን ጌይ" ተማሪዎች ለዘጠኝ ቀናት ያክል በክብረ በዓሉ እለት የሚሰባብሩዋቸውን ቅሎች በየቤቱ እየዞሩ፣ እየጨፈሩና መልካም ፀባይ የነበራቸውን የመሐመድ የልጅ ልጅ የሆኑትን የሐሰንና ሑሴንን ስም እየጠሩ ቅሎቹን ያሰባስቡ የነበረ ሲሆን ያሰባሰቡዋቸውን ቅሎች በስተው በመቃ ላይ ሰክተው ያከማቿቸዋል፡፡ በክብረ በዓሉ እለት ምሽት አካባቢ ዊርሻቶ የሚሉትን ባህላዊ ጭፈራ በጋራ እየጨፈሩ እና መጥፎ ስነምግባሮችን እያወገዙ እና እየኮነኑ

በቅድሚያ ያሰባሰቡዋቸውን ቅሎች ይሰባብራሉ፡፡ በመቀጠልም በቡድን በቡድን በመሆን ዊርሻቶን እየጨፈሩ ከቤት ወደቤት በመዘዋወር ክብ ሰርተው የያዙትን ዱላ መሬት ላይ በማጋጨት ቀደም ሲል የመዋፎ ስነምግባር መገለጫ የሆነው መጠዋ የሚዘጋጅበት እቃ ተምሳሌት አድርገው የሚሰባብሩትን ቅል እንዲወረወርላቸው ይጠይቃሉ፡፡ ጨፋሪዎቹ የሄዱባቸው እማወራዎች ቅሎችን እያወጡ ሲወረውሩላቸው እየተሻሙ ይሰባብሩታል፡፡ ወጣቶቹ በጭፈራቸው የመልካም ስነምግባር ተፃራሪ የሆኑት ጠጪነትን፣ ሱሰኝነት እና እነሱ የሚያስከትሏቸውን ማህበራዊ ቀውሶችን ከማውገዝና ከመከነናቸውም በተጨማሪ ተከታዩ አመት የተሻለ እንዲሆንላቸው ምኞታቸው የሚገልጹበት ክብረ በዓላቸው ነው፡፡



በዊርሻቶ ቁፈራ ወቅት ከሚዜሙት ስንኞች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

ዊርሻቶ ዊርሽ የሰበር

ዊርሻቶ ገል የሰበር

ኤሔር ዓሙት አሹራኸም ያቦርደሁ

አሎው ዓሙት ዓሙት ዞም ያቦርደኹ

ኢህዝናም የሊቅለኹ

ኢሂትዚኛም ተሊቀለኹ

አባዬ ሀሰንዚታ ሑሴን ዚታ ሊጂ የስጠሽ

ኡሞው ዚኢማን ረጋ

በርቲ ዚኛው ደሳጊዋ

ዴራ ደፍደፍ

ዊዚእ ጨፍጨፍ

<u>ተዛማጅ ትርጉሙ የሚከተለው ነው፣</u>

ዊርሻቶ መጥፎ ልማድ ይሰበር

ውሽት ውሽት ይሰበር

መጥፎ ገንቦ ይሰበር

በአዲሱ አመት አሹራ ኸም የምስራች ይሁንልን

አመት አመት ያድርስልን ሺ አመት ይስጥልን

እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ይደጉልን

እማዬ የሀሰንና ሁሴን እምሳያ መንታ ይስጥዎት

ትሁትና መልካም ፀባይ ያላቸው ያድርግልዎት

ኢማን ያላቸው ልባቸው የረጋ ይሁንልዎት

በላብ ተዘፈቀን ድካሙም በረታብን

እማማ ኳዳ በርብረው ቅሉን ይጣሉልን - የሚሉትን ስንኞች ደጋግመው ያዜማሉ፡፡

በክብረ በዓሉ እለት ከሚከናወኑት ተግባራት ሌላኛው ገንፎ የመብላት ሥነ-ሥርዓት ይገኝበታል፡፡ ገንፎ በእያንዳንዱ የብሔረሰቡ አባላት ቤት የሚዘጋጅ ሲሆን ገንፎው ከበሰለ በኋላ የፍየል ስጋ ተቆራርጦ ይጨመርበታል፡፡ ገንፎው የብሔረሰቡ አባላት ክብረ በዓሉ የሚውልበትን ወር  እና ለአስር ቀናት ከጾሙ

በኋላ ጾሙን ሲፈቱ ተሰባበስበው በጋራ የሚመገቡት ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላት በቤተሰብ ደረጃ ተሰባስበው ገንፎውን ከመብላት በተጨማሪ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው እና ለጎረቤቶቻቸው ገንፎ ወስዶ ማብላት የቆየ ልማዳቸው ነው፡፡ ከገንፎ መብላት ጋር ተያይዞ የሚነገረው አፈ-ታሪክ መሰረት በእለቱ እያንዳንዱ ሰው ገንፎ እስኪጠግብ መብላት ይኖርበታል፡፡ በእለቱ ገንፎውን ጠግቦ ያልበላ ሰው አመቱን ሙሉ ይራባል ተብሎ ስለሚታመን ገንፎ እስኪጠገብ መብላት ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባር መሆኑ ይነገራል፡፡

ሌላው የዚህ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ መገለጫ የብሔረሰቡ አስደናቂ ክንዋኔ ከዱር እንስሳት አንዱ በሆነውና በልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦች ድምጹ ሳይቀር የልጆች ማስፈራሪያ ተደርጎ የሚወሰደውን ጅብ ገንፎ የመመገብ ሥነ-ሥርዓት የዚህ ክብረ በዓል ሌለኛው መገለጫ ነው፡፡ ይህ ልማድ የተጀመረበትን አፈ-ታሪክ በተመለከተ አስረጂዎች ሲናገሩ ቀደም ባለው ጊዜ የአካባቢው ጅቦች የቤት እንስሳትንና ሰዎች ይተናኮሉና ይበሉ ስለነበረ የብሔረሰቡ አባላት ጅቦቹን ይገድሉዋቸው እንደነበረና ይህን ሁኔታ ለማስቀረት የሀገር ሽማግሌዎች በፈጠሩት መላ መሰረት ጅቦችን በዚሁ የክብረ በዓሉ መከበሪያ ቀን ማታ ገንፎ በማብላት የተፈጠረው እርቅ ቀጥሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ዛሬ ድረስ በጅቦችና በሰዎች መካከል ያለው ሰላማዊ ግንኙነት እንደቀጠለ ይነገራል፡፡

ጅቦችን ገንፎ በማብላት ሥርዓት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሲሆን በዚህም መሰረት ጅቦቹ ገንፎ በሚበሉበት አድባራት አካባቢ ያሉ እናቶች አንድ ላይ በመሆን በትላልቅ የገንፎ ማገንፊያ ብረድስቶች ገንፎውን ያገንፋሉ፡፡ የተቀሩት ሴቶች ደግሞ እያጨበጨቡ ስለክብረ በዓሉ ይዘፍናሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ጅቦቹን ገንፎ የሚያበሉ አባቶች ዘመኑ የሰላምና የጤና እንዲሆን ይፀልያሉ፡፡ ገንፎው በሚገባ እንደበሰለ ሴቶቹ ከብረድስቱ እየቀነሱ በማውጣት በትሪ ላይ በማድረግና መሀሉን ለቅቤ ማድረጊያ በእጃቸው ጫን ጫን በማለት ያጎደጉዱታል፡፡ በመቀጠልም ገንፎውን በእራሳቸው ላይ ተሸክመው ጅቦቹ ወደሚመገቡበት አድባራት በመውሰድ ጅቦቹ በሚመገቡበት የድንጋይ ቆሬ(ጎድጓዳ መመገቢያ) ላይ ያስቀምጡና ለዚሁ የተዘጋጀውን ቅቤ ይጨምሩበታል፡፡ በመቀጠል የጅቦቹ መጋቢ አባት በቅድሚያ የጅቦቹን ንጉስ ይጠራዋል፡፡ አስረጂዎች እንደሚሉት የጅቦቹ ንጉስ በቅድሚያ ብቻውን ወደተዘጋጀው ገንፎ በመቅረብና በመቅመስ የተጨመረው ቅቤ ያነስ ሆኖ ካገኘው ወደመጣበት እንደሚያፈገፍግና ነገር ግን ቀላቢው ወዲያው ቅቤ ሲጨምሩበት ተመልሶ በመምጣት ገንፎውን እንደሚቀምስና ሌሎች ጓደኞቹን በመጥራት ገንፎውን በጋራ ሆነው እንደሚበሉት ይነገራል፡፡ በዚሁ ጊዜ ጅቦቹ የቀረበላቸውን ገንፎ ግማሹን ከበሉ መጪው አመት የሰላም፣ የጤናና የጥጋብ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ጅቦቹ ገንፎውን ካልበሉ ወይም በተቃራኒው ጥርግ አርገው ከበሉ ግን ዘመኑ መጥፎ እንደሚሆን ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ጅቦቹን የማብላት ሥነ-ሥርዓት እንደተጠናቀቀም የየአድባራቱ ሀላፊዎች ዓመቱ መልካም እንዲሆንላቸው በመመኘትና በመመረቅ ጅብን ገንፎ የማብላት ሥርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

በሐረር ከዚህ ክብረ በዓል ጋር በተያያዘ ጅቦችን ገንፎ ከማብላት በተጨማሪ ዛሬም ድረስ በየምሽቱ ጅቦችን በተወሰኑ የከተማው አካባቢዎች በማሰባሰብና ስጋ የማጉረስ ትርኢትን የሚያከናውኑ ግለሰብ ተግባሪዎች ያሉ ሲሆን ቀደም ሲል ስጋውን ለጅቦቹ የሚሰጡት እነዚህ ተግባሪዎች ብቻ የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ሌሎች የትርኢቱ ተሳታፊዎች ከተግባሪዎቹ ጎን በመቀመጥና ለጅቦቹ ስጋ በመስጠት እራሳቸውን ሲያዝናኑ እና ማስታወሻ ፎቶዎችን ሲነሱ ይስተዋላል፡፡ በቀደመው ዘመን ከጅቦች ጋር የተፈጠረው እርቅ ዛሬ ለክልሉ ተጨማሪ የቱሪስት መስህብ ሆኖ ገቢ በማስገኘት በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ትርኢት የሚከናወነው በምሽት በመሆኑ ወደከተማዋ የሚመጡ ቱሪስቶች ከቀን ውሎአቸው በተጨማሪ ቢያንስ አንድ ምሽት ይህንን ትርኢት ለመመልከት በከተማዋ እንዲያሳልፉ እድል ፈጥሯል፡፡



## 2.5 የቅርሱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ( Significance of the Intangible Cultural Heritage)

ይህ ክብረ በዓል የብሔረሰቡ የማንነቱ መገለጫ ኢንታንጀብል ቅርሱ ከመሆኑም ባሻገር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ የብሔረሰቡ አባላትና ከብሔረሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩት የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ የሆኑት የኦሮሞ ብሔረሰብ አባላት በክብረ በዓሉ አማካኝነት በጾምና በፀሎት ከአምላካቸው ጋር የሚገናኙበት ከመሆኑም በላይ በመልካም ተግባራቸው ያለፉትን ነቢያትን የሚዘከሩበት በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ጠቀሜታ አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክብረ በዓሉ አንዱ ሥነ-ሥርዓት በሆነው ባህላዊ ጭፈራ እና የቅል ሰበራ ላይ ከብሔረሰቡ ተወላጆች በተጨማሪ በከተማዋ የሚገኙ የልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰብ ተወላጆች ጭምር ተሳታፊ በመሆናቸው የተነሳ የእርስ በእርስ ትስስርን በማጠናከርና ለመልካም ስነምግባር ተፃራሪ የሆኑት ተግባራት የሚወገዙበት በመሆኑ የአስተማሪነት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል፡፡ የክብረ በዓሉ ጠቀሜታ በዚህ ብቻ ሳይወሰን በቅል ሰበራው የተሳተፉ ወጣቶችን በጋራ ገንፎ እንዲበሉ በማድረግ፣ እንዲሁም በዚሁ ጊዜ የክብረ በዓሉ የተዘጋጀውን ገንፎ ከዘመድ አዝማድና ከጎረቤቶቻቸው ጋር ተጋርተው መብላታቸው ለዘመናት የቆየው የብሔረሰቡ ጠቃሚ እሴት እንዲሆን አስችሎታል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከክብረ በዓሉ ጋር ተያይዞ ጅቦችን በልዩ ልዩ አድባራት ገንፎ ለማብላት አስፈላጊ የሆነውን እህል ሰዎች በጋራ ማዋጣታቸውና በጋራ ሆነው አገንፍተው ማብላታቸው በሰዎች እና የዱር እንስሳት መካከል ሰላማዊ ግንኙነት የፈጠረ እና ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ምን ህል ተስማምተው መኖር እንደሚችሉ በማሳያነት ሊጠቀስ የሚችል ክንዋኔ መሆኑ የቅርሱን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ የበለጠ ያጎላዋል፡፡

# 3. የቅርሱ መለያ ባህርያት( Characteristics of the element)

## 3.1 የቅርሱ ቁሳዊ መግለጫ(Associated tangible aspect)

የቁራን ጌይ ተማሪዎች ቀደም ሲል በነበረው ልማድ ዊርሻቶ /ባህላዊ ጭፈራ/ እና የቅል ሰበራ ክብረ በዓል ሊከበር 9 ቀናት ሲቀሩት በተከታታይ በክብረ በዓሉ እለት የሚሰባብሩትን ቅል አሰባስበው ትምህርት ቤታቸው ውስጥ ያስቀምጣሉ፡፡ ለቅል ሰበራው የሚጠቀሙበትንም ዱላ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በክብረ በዓሉ የሚበሉትን ገንፎ ለማዘጋጀት ሴቶች ምስር፣ አተር፣ ሽምብራ፣ ስንዴ እና ሌሎችንም ለገንፎው የሚያስፈልጉ እህሎችን ለቅመውና፣ ፈጭተውና ፈትገው በፀሐይ እንዲደርቅላቸው በአካባቢው የሚሰሩዋቸውን ሰፌቶች ይጠቀማሉ፡፡ ስንዴውንም ለመፈተግሙቀጫ እና ዘነዘና ይገለገላሉ፡፡ ገንፎውንም ለማገንፋት ትላልቅ ድስቶችን እና ማማሰያ እንዲሁም ገንፎው ከተገነፋ በኋላ የሚያወጡበት ከብረታ የተሰራን ትሪ ወይም ከእንጨት የተሰራ ቆሪን ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀይማኖት አባቶች በበአሉ ቀን ተስማሚ የሆኑ አልባሳትን የሚለብሱ ሲሆኑ የብሔረሰቡ ሴቶች ደግሞ በዛው አካባቢ የሚዘጋጀውን ገኖፊ/ሱሪ/ ከስር አድርገው ከላይ ሰፊ ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ በላዩም ላይ ጥቁር ቀለም ያለውና ሰፊ አላባሽ/ሸናዊ/ ይደርባሉ፡፡ ፀጉራቸውንም በሻርፕ/ንዚፋ/ይሸፍናሉ፡፡

በማንባራቸው ላይ እነሱ ዘርግፍ የሚሉትን ጌጥ የሚያደርጉ ሲሆኑ፣ በጆሮአቸው ላይ ደግሞ ኡዙን ቢልቢላ የሚሉትን የጆሮ ጉትቻ እንዲሁም በክንዳቸው ላይ ሻንኬት በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን የእጅ አምባር ያደርጋሉ፡፡ ወጣቶች በበኩላቸው የአዘቦት ልብሳቸውን ለብሰው በክብረ በአሉ ላይ ይታደማሉ፡፡

### 3.2 የቅርሱ አካላዊ መገለጫ (Associated intangible Aspects)

በክብረ በዓሉ ጋር አተገባበር ወቅት ልዩ ልዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና ሥነ-ሥርዓቶች ይከናወናሉ፡፡ ቀደም ሲል እንዳልነው በበአሉ ወቅት ለሰበራ የሚውሉ ቅሎችን ለማሰባሰብ ወጣቶች ቀደም ብለው ከቤት ወደቤት እየዞሩ ቅሎችን ከየቤተሰቡ እየጠየቁ ያሰባስባሉ፡፡ በበአሉ እለት ምሽት ላይ በቅድሚያ የቁራን ጌይ ተማሪዎች ቀደም ሲል ያሰባሰቡዋቸውን ቅሎች በትምህርት ቤታቸው ግቢ ዊርሻቶ የሚለውን ባህላዊ ዘፈን እየዘፈኑና ለመልካም ስነምግባር ተፃራሪ የሆኑ ምግባራትን እየኮነኑ ያሰባሰቡዋቸውን ቅሎች ይሰባብራሉ፡፡ በመቀጠልም ወጣቶቹ እየጨፈሩና እያዜሙ ከቤት ወደቤት በመሄድ እማወራዎችና ሴቶች የሚጥሉላቸውን ቅሎች እየተሻሙ ይሰባብራሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በዊርሻቶ ጭፈራ ላይ የተሳተፉ ወጣቶችንና ሌሎችንም ገንፎ ለማብላት የብሔረሰቡ ሴቶች ከስንዴ እና ከሌሎች እህሎች የገንፎ ዱቄት አዘጋጅተውና አገንፍተው ዘመድ አዝማድና ጎረቤት ተሰባስቦ ገንፎውን በጋራ ይመገባሉ፡፡ በሌላም በኩል በዚሁ እለት ምሽት ጅቦችን ገንፎ የማብላት ሥርዓት የሚከናወን ሲሆን በየአድባራቱ አቅራቢያ የሚገኙ ሴቶች በጋራ ተሰባስበው ገንፎውን የሚያዘጋጁ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ እያጨበጨቡ ይዘፍናሉ፡፡ በመጨረሻም ገንፎውን ጅቦቹ ወደሚበሉባቸው ቦታዎች ካኗኗሡ በኋላ መጋቢዎቹ በቅድሚያ የጅቦቹን ንጉስ የሚጠሩበትና ጅቡም መጀመሪያ ብቻውን መጥቶ የተዘጋጀውን ገንፎ በመቅመስ በቂ ቅቤ ካልተደረገበት ወደኋላ የሚያፈገፍግበት ሁኔታ፣ ቀጥሎም መጋቢዎቹ በቂ ቅቤ ካደረጉ በኋላ ተመልሶ የሚመጣበትና ቀጥሎም ሌሎች ጅቦች እንዲመጡ የጥሪ ድምጽ ሲያሰማ ጅቦቹ የሚሰባሰቡበትና በጋራ የሚመገቡበት ሁኔታ ሌለኛው የቅርሱ አካላዊ መገለጫ ነው፡፡ በዚሁ እለትም በየአድባራቱ ዘመኑ የሰላም የጤና እንዲሆን የሚከናወነው የምርቃት ሥነ-ሥርዓት ሌለኛው የቅርሱ አካላዊ መገለጫ ነው፡፡

## 4. ኢንቨንተሪ ከተደረገው ቅርስ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት፣

### 4.1 የቅርሱ ተግባሪዎች/አከናዋኞች/ Practitioner/s/Performer/s/፡-

ቅርሱን የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚተገብሩት ሲሆን ቀደም ሲል የሐይማኖት ትምህርት ቤቶች የሆኑት ቁራን ጌይ ትምህርት ቤቶችና መድረሳዎቻቸው፣ አሁን ደግሞ በከተማው ውስጥና ዙሪያ የሚገኙ የብሔረሰቡ እና የሌሎች ብሔረሰቦች ወጣቶችና ታዳጊዎች፣ ሴቶች፣ አባቶች የየአድባራቱ ሀላፊዎችና የሀገር ሽማግሌዎችና የሀይማኖት አባቶች እንዲሁም ጅቦች የቅርሱ ተግባሪዎች ናቸው፡፡

### 4.2 ሌሎች ተሳታፊዎች/ጠባቂዎች/Other participants (custodians/holders) ፡-

የክልሉ የባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ፣ የከተማውና እና የዙሪያዋ የፖሊስ ሰራዊት አባላት፣ የክልሉ አስተዳደር እና በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር አካላት የቅርሱ ጠባቂዎች እና ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

4.3 ቅርሱን ለማየት ወይም ለመድረስ ያሉ ሥርዓቶችና ደንቦች (Customary practices governing access to the element or to aspect of it)

ለክብረ በዓሉ የሚዘጋጀውን ገንፎ ሴቶች እንዲሁም ወንዶች በጋራ እና በተናጠል የሚመገቡት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጅቦቹን ገንፎ ለማብላት በእድሜያቸው ከፍ ያሉ እና በህብረተሰቡ የተለየ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው አባቶች ብቻ ለጅቡ ጥሪ በማድረግ የሚመግቡት ከመሆኑ በተለየ ቅርሱን ለማየትም ሆነ ለመድረስ የተለየ ስርዓትና ደንብ የለም፡፡



## 5. የቅርሱ ቀጣይነትና ደህንነት/ቅርሱ የሚገኝበት ሁኔታ(State of the element)

### 5.1 ቅርሱ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ(Current state of the element)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባጎናፀፈው መብት መሰረት የሐረሪ ብሔረሰብ ውርሻቶችንና ሌሎች አመታዊ ክብረ በዓላትን እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ክብረ በዓሉ ከጊዜ ወደጊዜ እንደቀድሞው እየተተገበረ እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሰው ደግሞ ቀደም ሲል በተጠናከረ ሁኔታ የእስልምና ባህላዊ ትምህርት ይሰጥባቸው የነበሩት የቁራን ጌይ ተቋማት ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከሙ በመሄዳቸው የተነሳ ተማሪዎቻቸው/መድረሳዎች/ እንደቀድሞው በበአሉ እለት የሚሰባብሩትን ቅል ቀደም ብለው የማሰባሰቡን ሁኔታ እየተገበሩት አለመሆናቸው ይነገራል፡፡ ይህ ከትምህርት ቤቶቹ መዳከም በተጨማሪ ቀደም ሲል እንደልብ ይገኙ የነበሩትን ቅሎች በአሁኑ ወቅት ማግኘት አለመቻሉም ሌለኛው ምክንያት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ ከከተማዋ ክልል ወጣ ብሎ ጅቦችን በእለቱ ገንፎ የማብላቱ ሥርዓት እየተዳከመ ሲሆን የዚህም መነሻው ከእምነት ጋር በተያያዘ ጅቦችን ገንፎ ማብላቱና ጅቦቹ ገንፎውን በልተው ከመጨረሳቸውና ካለመጨረሳቸው ጋር ተያይዞ ስለቀጣዩ አመት አባቶች የሚሰጡትን ትንቢት ተገቢነት ላይ ጥያቄ የሚያነሱ እና ተቃውሞ የሚያሳዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች እየተፈጠሩ ከመሆኑ ጋር ጅቦቹ ወደቦታው እንዳይሄዱ የማድረግ አዝማሚያ በመስተዋሉ ጅቦችን ገንፎ የማብላት ልማዱ እንደቀድሞው ጊዜ እየተተገበረ አይገኝም፡፡ በሌላም በኩል የዊርሻቶ/ባህላዊ ጭፈራም/ ይዘት በተወሰነ ደረጃ እየተቀየረ በመምጣቱ በቅርሱ ክዋኔ ላይ ለውጥ መስተዋሉ ይነገራል፡፡ ሆኖም እነዚህን መሰል ጉድለቶች ቢስተዋሉም በአሉ በየአመቱ እተተገበረ ይገኛል፡፡

### 5.2 ቅርሱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገዶች( Mode of transmission from generation to generation)፡-

ዊርሻቶ እና በዚሁ እለት የሚተገበሩት ሌሎች ክንውኖች የብሔረሰቡ የማንነት መገለጫ በመሆናቸው ክንዋኔዎቹ እየተተገበሩ እንዲቀጥሉ የብሔረሰቡ አባላት የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተለይም ቅርሶቹን በመተግባርና ሲተገበሩም መልእክቶችን በማስተላለፍና ቀጣዩ ትውልድ መተግበሩን እንዲቀጥል እያበረታቱ ይገኛሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በሁሉም ዕድሜ የሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት ፆታ ሳይለይ በዊርሻቶ ጨዋታ እና በሌሎች ክንዋኔዎች ላይ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ፍጻሜው በመሳተፍና በመተግበር ለምሳሌ ወጣቶች የዊርሻቶን ጭፈራ እየጨፈሩ ከቤት ወደቤት እየተዘዋወሩ የሚሰጣቸውን ቅል ሲሰብሩ በየቤተሰቡ ያሉ ሴቶች ደግሞ ወጣቶቹ እየጨፈሩ ሲመጡ ቅሎቹን በማሻማት እንዲሰብሩ በማድረግና በመጨረሻም ገንፎ አዘጋጅተው በማብላት ቅርሱ እየተተገበረ እንዲቀጥል ያደርጋሉ፡፡ በዚሁ ጊዜም ሁሉም በምልከታ እና በትግበራ ዘዴ ስለ ኢንታንጀብል ቅርሱ አተገባባር ይማራሉ፣ በተጨማሪም ጨፋሪዎቹ የመልካም ስነምግባር ተጻራሪ የሆኑ ተግባራትን በሚያሰሙዋቸው ስንኞች ሲያሰሙ ሌሎች

የህብረተሰብ ክፍሎች ከመሰል ተግባራት እራሳቸውን እንዲከላከሉ ትምህርት የማስተላለፍ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በዚህም ኢንታንጀብል ቅርሱ ለመጪውም ትውልድ እየተላለፈ ይመጣል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሐንን በመጠቀም የክልሉ ባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ስለ ክብረ በዓሉን ለማስተዋወቅ የሚያከናውናቸው ተግባራት ቅርሱ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ የሚያስችሉ ተግባራት ናቸው፡፡

## 5.3 ቅርሱን ለመተግበር ያሉ ስጋቶች( Threats to the enactment)

### 5.3.1 አካላዊ ወይም ቁሳዊ ስጋት(Physical threats):-

የዊርሻቶ በዓል ዋነኛ መገለጫው ከሳምንት ላላነሳ ጊዜ የቁራን ጌይ ተማሪዎች ቅል የሚያሰባስቡ የነበረ ሲሆን እነዚህ ባህላዊ የትምህርት ተቋማት ወደ መዋዕለ ሕፃናት በመቀየራቸው የተነሳ እንዲሁም ከአካባቢ ስነምህዳር ላይ በታየው ለውጥ  እና ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ገበሬው ያለችውን ውስን መሬት ለገበያ ምርቶች ማምረቻነት በመጠቀሙ የተነሳ እንደበፊቱ ሰፊ ቦታ የሚይዙ የቅል ተክሎች ለማብቀልና ፍሬ ለማፍራት የሚችሉበት ሁኔታ ተመናምኗል፡፡ በሌላም በኩል በቅሎቹ ምትክ ህብረተሰቡ ልዩ ልዩ የፕላስቲክ ምርቶችን ለአገልግሎት ስለሚጠቀም የቅል ተፈላጊነትና በቅል መጠቀም በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ በዚህም የተነሳ ሲሰበር የተለየ እርካታን የሚሰጠው እና በቀላሉ የሚሰበረው ቅል  እንደልብ አለመገኘት በቅርሱ አተገባበር ላይ የተስተዋለ ቁሳዊ ስጋት ነው፡፡ በሌላም በኩል ከጊዜ ወደጊዜ በተፈጠረው የኑሮ ውድነት የተነሳ በሁሉም አድባራት ለጀቦች ቅቤ የማብላት ልማዱ እየቀነሰ መሄድ ተስተውሎበታል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ ያሉ የተወሰኑ አስተምህሮቶች በተለይ ለጅብ ገንፎ ማብላቱንና ከዚሁ ጋር ተያያዞ በአባቶች ስለቀጣዩ አመት የሚሰጡ ትንበያዎችን ከፈጣሪ አስተምህሮት ጋር ይቃረናል በሚል ሥርዓቱ እንዳይካሄድ የሚያደርጉበትና በተቃራኒው ማስተማራቸው ሌለኛው በቅርሱ አተገባበር ላይ የተስተዋለ ስጋት ነው፡፡

### 5.3.2 ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስጋቶች (Socio- economic threats)

በዘመናዊ ትምህርትና አስተሳሰብ፡ ግሎባላይዜሽን/ሉላዊነት በሚያሳድሯቸው አሉታዊ እና አዎንታዊ ተጽእኖዎች የተነሳ ወጣቶች ለተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተጋላጭ በመሆናቸው የተነሳ ለባህላዊ ክንዋኔዎች የሚሰጡት ትኩረት ከጊዜ ወደጊዜ እየላላ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህ መገለጫዎች አንዱ የሆነው እና በዓሉ ሲከበር በሚጨፈረው ባህላዊ ጭፈራ /ዊርሻቶ/ ውስጥ ይሰሙ የነበሩ ስንኞች  ከዘመን አመጣሽ ስንኞች ጋር እየተደባለቁና እየተቀየሩ መስማታቸው ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ በሌላም በኩል ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ለበዓሉ ድምቀት ከሚያጎናጽፉት ክንውኖች መካከል የብሔረሰቡ ተወላጆች በቤተሰብ ደረጃ እና ከዛም አልፎ ከአጎራባቾች ጋር በመሆን በጋራ ገንፎ የሚበሉበት ሥርዓት ተጠቃሽ የነበረ ቢሆንም በጊዜ ሂደት በአሉን በጋራ የማክበሩ ልማድ በተወሰነ ደረጃ መቀነስ እንደተስተዋለበት

ይነገራል፡፡ እነዚህ ስጋቶች ቅርሱ እየዳበረ እና እየተስፋፋ ከትውልድ ወደትውልድ የመሸጋገር እድሉን በተወሰነ ደረጃ እንዲላላ እና እንዲቋረጥ ሊያደርገው እንደሚችል ይገመታል፡፡

### 5.4 ለቅርሱ ቀጣይነት እየተደረጉ ያሉ እንክብካቤዎች(Safeguarding measures in place)፡-

የክብረ በዓሉን አመጣጥና የሚከበርበትን መሰረታዊ ምክንያት የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሐይማኖት አባቶች እንዲሁም እናቶች ለልጆቻቸው የሚነግሩና ምክር የሚሰጡ ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን በበዓሉ አከባባር ወቅት ክንውኖቹን በተግባር በማሳየት ቅርሱ እየተተገበረ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ የጎላ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሀብረተሰቡ ከሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ጥረቶች ጎን ለጎን የክልሉ መንግሥት የባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ቅርሱ እየተተገበረ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ በእሉን አስመልክቶ ጥናቶችን በማድረግ፣ ብሮሸሮችንና ፖስተሮችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሰፊ የማስተዋወቅ ስራ እና የዶክመንቴሽን ስራ እያከናወነ ሲገኝ ለዚህም የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቢሮው ቅርሱ በዩኔስኮ የአስቸኳይ ጊዜ የጥበቃ ዝርዝር( Urgent Safeguarding List) ውስጥ እንዲካተት እራሱ ተነሳሽነትን በመውሰድ እና ከፌዴራል ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ለዊርሻቶ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ እንክብካቤ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 6. የመረጃ አሰባሰብና ጥንቅር(Data gathering and inventorying)

### 6.1 በኢንቬንተሪው ወቅት የሕብረተሰቡ፣ የቡድኖችና ግለሰቦች ተሳትፎ መገለጫዎች( Consent from and involvement of the community/group in data gathering and inventorying)፡-

የዊርሻቶ ክብረ በዓል ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስ ኢንቬንተሪ በተከናወነበት ወቅት በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት በየእርከኑ የሚገኙ እና ጉዳዩ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና መንግስታዊ አካላት፣ የብሔረሰቡ ተወላጅ ምሁራን፣ የሀገር ሽማግሌዎችና እናቶች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ሴትና ወንድ ወጣቶች ለኢንቬንተሪው መሳካት ሙሉ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ በተለይ ለኢንቬንተሪው መሳካት የክልሉ የባህል ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ አስተዋጽኦ ከፍተኛ የነበረ ሲሆን መገለጫዎቹም መረጃ አቀባዮችን በመለየትና በማስረዳት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበርና የኢንቬንተሪውን ስራ በመደገፍ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ነው፡፡

### 6.2 ኢንቬንተሪ የተደረገውን ቅርስ ለመጠቀም ያሉ ገደቦች(Restriction, if any, on use of inventoried data)፡-

ኢንቬንተሪ የተደረገውን ቅርስ የተመለከቱ መረጃዎችን በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በክልሉ ቅርሱን ለማስተዋወቅና ለብሔረሰቡ ባህል ዕድገት በግብአትነት መጠቀም ክልከላ የለውም፡፡ ነገር ግን መረጃዎቹን

ከዚህ ተጻራሪ በሆነ መንገድ በመተርጎምና በማባባት፣ በማባባት ለንግድና ትርፍ፣ የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ያለባለቤቶቹ ፈቃድ መጠቀም አግባብ ባለው ሕግ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

6.3 ምዝገባው የተካሄደበት ቀንና ቦታ(Date and place of data gathering)፡-

መጋቢት 24 ቀን 2005 (April 1, 2013) ዓ.ም በአገር አቀፍ የምዝገባ መለያ ቁጥር 0002 ተመዝግቧል፡፡

6.4 ቅርሱን በሀገር አቀፍ ደረጃ የመዘገበው አካል (Responsible body to the national inventory/register of the element)፡-

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ከሐረሪ ባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር ነው (Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage in cooperation with Harari Culture, Heritage &Tourism Bureau)

Ephraim Amare

Cultural Heritage Inventory and Standardization Director

The Federal Democratic Republic of Ethiopia * Ministry of Culture & Tourism * Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage